# "Fly out of Ethiopia while you can." ማለትስ አሁን ነው

አምባቸው ደጀኔ (ከወልዲያ)

ከተማ ይፍሩ የተባሉ የደርግ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚንስትር(?) ለሥራ ጉብኝት ወደ ውጭ ሄደው በዚያው ቀሩ አሉ፡፡ ለምን እንደቀሩ ሲጠየቁ በርዕሴ የጠቆምኩትን የእንግሊዝኛ ዐረፍተ ነገር እንደተናገሩ ይወሳላቸዋል - "አጋጣሚ ባገኘህ ጊዜ (ሁሉ) ከኢትዮጵያ ሽሽ!" ተብሎ ቢተረጎም ያስኬዳል- ህልምና እንግሊዝኛ ደግሞ እንደፈቺው ነው አሉ፡፡

ሀገራችን ካለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት ወዲህ በተለይ ለይቶላት ባለቤት አልባ ሆናለች፡፡ አሁን ያለው የዶ/ር አቢይ መንግሥትም ምን እያደረገ እንደሆነ እንኳንስ ሌላው ራሱ አቢይም የሚያውቅ አይመስልም፡፡ ሀገሪቱ መሽቶ ይነጋላታል እንጂ ያለመሪና ምናልባትም ያለ ሕዝብ በደመነፍስ እየተውገረገረች ነው - አለች ለመባል ያህል፡፡

ይህን የሚያስብሉ ጥቂት ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል፡፡

1. **የኑሮ ውድነት** - ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ ኑሮ ከመንኮራኩር በሚልቅ ፍጥነት ወደ ሰማየ ሰማያት ሲመጥቅ "ይህ ሕዝብ የኔ ሕዝብ ነው፤ በኑሮ ውድነት ሲጠበስ፣ ከገቢው ጋር የማይመጣጠን የኑሮ ውድነት በእሳት አለንጋ ሲገርፈው እኔን በዋናነት ይመለከተኛልና ገበያውን ላረጋጋ፤ ንግዱን ልቆጣጠር፤ የንግዱን ማኅበረሰብም ንቃተ ኅሊናውን አሳድጌ ተመጣጣኝ ትርፍ እንዲያገኝ ላስችል፤ ኢኮኖሚውና ሕዝብ እንዲገናኙ ላድርግ...." የሚል መንግሥትም ሆነ የመንግሥት አካል አልተገኘም፡፡ ሁሉም ሩጫው የራሱን ኑሮ ለማመቻቸት ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው ሕዝቡም ሆነ ሀገሪቷ የኔ ናቸው የሚላቸው አካል አለመኖሩን ነው፡፡ የመኪና ባትሪ በ10 ዓመታት ውስጥ ከብር 300 አሁን ወደ ብር አምስት ሽህ ሲገባ፤ አንድ ዕንቁላል ከስሙኒ ወደ 6 ብር ሲገባ፤ ኩንታል ነጭ ጤፍ ከብር 1000 ገደማ ወደ ብር 4000 ሲጠጋ፣አንድ ሊትር ዘይት ከብር 12 ወደ ብር 90 ሲሸቀነጠር፣ የ20 ብር የቀን ሠራተኛ (ወዛደር) ወደ ብር 400 እና ከዚያ በላይ ሲመነደግ፣ የቤት ሠራተኛ ከ50 እና 60 ብር ወደ ብር 2500 ሲያሻቅብ፣ ለትንንሽ የመኪናም ሆነ የቤት ጥገናዎች ይወጣ የነበረው ብር 300 እና 500 አሁን ከአሥር ዕጥፍ በላይ አድጎ ብር 3000 እና 5000 ሲገባ (በጣም ትንሽ ጥገና ነው! ሞተር ላውርድ ካልክ የዛሬ 10 ዓመት መኪናውን የገዛህበትን ዋጋ የሚያስከነዳ ዋጋ ትጠየቃለህ፤ የቀን ጅብ ሆኗል እያንዳንዱ ባለሙያና የንግድ ድርጅት፡፡ አቢይ ሲያቀብጠው "የቀን ጅብ" አለ ያኔ፡፡ እነዚያኞች መቀሌ ሲመሽጉ ሌሎች የቀን ጅቦች በየቀኑ እዚሁ ይፈለፈሉ ገቡ)..... ይህ ሁሉ ምስቅልቅል በሀገር ላይ ባልተለመደ ሁኔታ ሲከሰት ታዲያ የኢትዮጵያ መንግሥት ነኝ ባዩ የአቢይ መንግሥት እየታዘበ ቁጭ ከማለት ወይም ምናልባትም ለተለዩ ውስጣዊ ተልእኮ ሲባል ለኑሮው መመሰቃቀል የበኩሉን አስተዋፅዖ ከማድረግ ውጪ ሊያደርግ የሞከረው አንድም ነገር የለም፡፡ "የኔ ነው" የምንለው መንግሥት እንደማጣት ያለ ቁጭት የሚለቅ ነገር ደግሞ የለም፡፡ እኔ ቤተሰቤ ሲራብና ሲጠማ የማይሰማኝ ከሆነ ደደብና ደንቆሮ ነኝ ማለት ነው፡፡ ኃላፊነቱን የማያውቅ ወላጅና መንግሥት አንድ ናቸው፡፡ ስለሆነም ነው የአቢይ መንግሥት የኔ መንግሥት የማይመስለኝ፡፡ ደንቆሮና ዕውር መንግሥት ካላቸው ሀገሮች ቀዳሚዋና ምናልባትም ብቸኛዋ ሀገር ኢትዮጵያ ናት - "አከሰሱ" ያላችሁ አንድ ዜጋው እንዲህ ማለቴን ንገሩት፡፡ ይሄ ነገር በጣም ይገርመኛል፡፡ በርሀብና በርዛት፣ በበሽታና በቁሮ ማለትም በህግ-አልባዎች የዝርፊያና ግድያ ቡድን አንቀጥቅጦ መግዛት ወንጀል ነው፡፡
2. ሥርዓት አልበኝነት - አሁን ይህችን ማስታወሻ እየጻፍኩ እንኳን በመስኮት መንገዱን ስመለከት መሀል አዲስ አበባ ላይ ወጣቶች መንገዱን ዘግተው በኦሮምኛ ቋንቋ እየዘፈኑና እየጮኹ ነው፡፡ መጮኻቸውን አልቃወምም፤ መብትም የለኝም፡፡ ግን መንገድ እየዘጉና የትራፊክ እንቅስቃሴን እያወኩ በሥራ ሰዓት እንዲህ መሆን አግባብ አይደለም፡፡ ይሄ "ጊዜው የኛ ነው!" የሚሉት ዘመን አመጣሽ ፈሊጥ ሀገራችንን የለየላት ሦርያና ሶማሊያ ሳያደርጋት በሀገራችን ህጋዊና ብሔራዊ ስሜት የሚሰማው ሕዝባዊ መንግሥት መቆም ይኖርበታል፡፡ በየክልሉ ሄደን ብናይ መንግሥት ያለ አይመስልም፡፡ ሁሉም ባፈተተው ይጓዛል፡፡ የማኅበረሰቡ ሕይወት በጎረምሦችና በወጠጤዎች የምሕረት እጅ ውስጥ ነው፡፡ አዲስ አበባም እንደዚሁ ናት፡፡ በህጋዊ መንገድ ጉዳይን ማስፈጸም ታሪክ ሆኗል፡፡ ጉቦና ሙስና ጫፍ ወጥተዋል፡፡ ለሀገርና ለወገን ማሰብ ዕርም በመሆኑ ሥራንና የሥራ ኃላፊነትን በአግባቡ መወጣት ቀርቷል፡፡ ሙስና የደም ሥር ከሆነ ሰነበተ፡፡ ምናልባት ሰዎች በእውነተኛ ገቢያቸው መኖር አለመቻላቸው ለዚህ ዓይነቱ ህገ ወጥ ድርጊት ዳርጓቸው ሊሆን ይችላል፡፡ መንግሥት ቢኖር ይህን ጉዳይ ግምት ውስጥ በማስገባት ከኑሮው ጋር የሚመጣጠን ደሞዝ እንዲከፈል ህግ ያወጣ፣ አዲ የደሞዝ አስኬልም ይቀርጽ ነበር፡፡ አሁን ግን ሀገራችን ባለቤት ስለሌላት እንዲያውም ይባስ ብለው ካለችንም ትንሽዬ ገቢ እንዴት እንደሚዘርፉ ያውጠነጥናሉ እንጂ ለኛ ኑሮ ግዴላቸውም፡፡ በዚህ ረገድ

ነጋደው በዓመት በሚሊዮኖች ለሚያስገባበት ንግድ በሙስና ትስስር ጥቂት ሽዎችን እንዲከፍል ሲደረግ የኔ ዓይነቱ ምሥኪን ደሞዝተኛ ላይ ቫትን ጨምሮ ከ50 በመቶ በላይ ከደሞዛችን ይቆረጣል፡፡ ጊዜው ሲደርስ የምናወራው የገቢዎች ሚኒስቴር በተለይ በሠራተኛው ላይ የሚፈጽመው ግፍና በደል እጅግ ብዙ ነው፡፡ ገና ለገና የመንግሥትን ገቢ አሳደግን ብለው የቅጥር ሠራተኞችን ደሞዝ ከየትኛውም የዓለም ሀገር በማይወዳደር የቀረጥ ዓይትና የአቀራረጥ ሁኔታ እየመዘበሩንና ኑሯንን መቅኖ እያሳጡት ይገኛሉ፡፡ ለነገሩ ቀረጥና ግብሩ እነሱን ስለማይካ ምን ያድርጉ፡፡ እነሱ እኮ ደሞዝ የሚከፈላቸው ለስሙ እንጂ የኑሯቸው መሠረት ሌላው ቀርቶ አንዱ ነጋዴ ብቻም ሊሆን ይችላል፡፡

3. **የባለሥልጣናት ድንቁርና** - ልብ አድርጉ፤ አጎቴና አክስቴ በባዶ እግራቸው የመሬት እሾህና የዛፍ ላይ ቆንጥር እያሰቃያቸው ተርበውና ታርዘው በሚከፍሉት ግብር በስምንትና አሥር ሚሊዮን ብር ቪ-8 መኪና መንግሥት ይገዛና ለየባለሥልጣናቱ ያድላል፡፡ እነሱም በነዳጁ፣ በአበሉ፣ በምኑም በምናምኑም የዚህን ምሥኪን ሕዝብ ገንዘብ ያሚጥጡታል፡፡ ለሕዝቡ ግን አንድም ነገር አይሠሩለትም፡፡ አብዛኛው ሕዝብ ውኃ የለውም፤ መንገድ የለውም፤ ትምህርት ቤት የለውም፤ ህክምና የለውም - ("ነቲንግ!" አለ ያ መንኜ በአንድ ንግግሩ - በጣም ተናዶ )፡፡ ገበሬው ከዛሬ 100 ዓመት በፊት የነበረውን ሕይወት እየመራ ባለሥልጣናቱ ግን የ21ኛውን መቶ ክፍለ ዘመን አውሮፓዊ ሕይወት ይቀጫሉ - ቀንቼ እንዳይመስላችሁ - ነገረ ሥራቸው ስለሚያናድድ እንጂ፡፡ በዚህም ቅንጣት አይሰማቸውም፡፡ ምክንያቱም ተፈጥሯዊ ድንቁርና ጆሯቸውንም ልቦናቸውንም የፊጥኝ አስሮታልና፡፡ ትንሽ መልካም ሥራ ቢሠሩ እንኳን እሰዬው ነበር፡፡ ግን አንዳችም የለም፡፡ ቢሯቸው እንኳን የሚገኙት ከስንት አንድ ናቸው፡፡ በየመሥሪያ ቤቱ የሚባክነውን ገንዘብና ሀብት ስታዩ፣ ላልተሠራ ፕሮጀክት ሳይቀር ብዙ ሚሊዮን በብድርና በምጽዋት የተገኘ ገንዘብ በሀሰት ሠነድ እየተወራረደ የሚጠፋውን የገንዘብ መጠን ስትሰሙ እንደ ኢትዮጵያዊ ከማሣፈሩም በተጨማሪ እንደ አንድ ጤናማ ዜጋ ያሳብዳችኋል፡፡ ይህን ኢትዮጵዊነት ምን እናድርገው ይሆን?

4. **የመንጋ ፍርድ** - በየአካባቢው የሚታዬው የመንጋ ፍርድ ኢትዮጵያ ውስጥ ለአንዲትም ደቂቃ ቢሆን እንድትኖር አያደርግህም፡፡ መውጫ ቀዳዳ ቢኖር ብዙ ዜጎች በአንድ ጀምበር ከኢትዮጵያ ውልቅ ብለው በተገላገሉ ነበር፡፡ በየትም ሥፍራ ብትሄድ እንደ ዘመነ ክርስቶስ "ስቅሎ፣ስቅሎ" ነው መመሪያው፡፡ ሰውን ዘቅዝቆ መስቀል፣ ሰውን ገድሎ ሬሣን ዘመድ እንዳይወስድ በመከልከል የግፍ ግፍ በጅብ ማስበላት፣ አባትን ከቤት ጠርቶ በልጆች ፊት መሀል አናትን በጥይት መፈጥፈጥ፣ ልጅን ገድሎ በሬሣው ላይ እናትን ማስጨፈር፣ ተደራጅቶ ገንዘብና ንብረት በመቀማትና በመዝረፍ የራስን ኑሮ ማበልጸግ፣ ጭቁን ዜጋ በላቡ የሠራውን ኮንዶምንየም ቀምቶ ለራስ ጎሣ ማደል፣ ከአንዱ አካባቢ ወደሌላው አካባቢ እህልና ጥራጥሬ እንዳይገባ ማገድ፣ ወዘተ. የሀገራችን ዘመናዊ ባህል ከሆኑ ሰነበቱ፡፡ ይህም የመንግሥትን ደካማነት ወይም ከፍ ሲል እንደጠቀስኩት የወንጀል ተባባሪነት ከማሳየት ባለፈ ሌላ ትርጉም ሊሰጠው አይችልም፡፡ ይህችን የመሰለች ሀገር እየመራሁ ነው ማለትም በእጅጉ ያሣፍራል፡፡ እኔ አቢን ብሆን በሚደረግልኝ የዲፕሎማሲ ፕሮቶኮል እሸማቀቅና ደብቁኝ እል ነበር፡፡ የዚህች ሀገር መሪ መሆን በምንም መንገድ ሊያኮራ አይችልም፤ አይገባምም፡፡ ኢትዮጵያ ያለች የምትመስለው አርትስ ቲቪን በመሳሰሉ አንዳንድ ገራገርና ጥሩ የሚመኙ ሚዲያዎች ውስጥ ብቻ እንጂ በእውን ኢትዮጵያ በቀደመው ይዘቷ አለች ማለት በፍጹም አንችልም፡፡ ልቀጥል ? ጊዜ የላችሁም መሰለኝ ... መልስ ለመስጠት ተጓደዳችሁብኝ፤ ስለዚህ ይቅርብኝ፡፡ ... ግን ሀገራችን እንዳለች የማትቆጠር መሆኗን ያዙልኝ፡፡